የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
FDRE PHARMACEUTICALS FUND AND SUPPLY AGENCY
የሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት
OFFICE OF BOARD OF DIRECTORS

ቁጥር ስአቦ/መፊአኤ/003/2009 ቀን 03/11/2009
Ref.No. Date

ለመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የስራ አመራር ቦርድ ያፀደቀውን የዋጋ አተማመን አፈፃፀም መመሪያ 21 ገፅ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን እየላክን መመሪያው ተፈፃሚ እንዲሆን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ቦጋለ ፈለቀ
የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ

አባሪ ፡- ከላይ እንደተገለፀው

ግልባጭ

✓ ለሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት

መ.ፈ.አ.ኤ

ስልክ Tel. 011- 276 32 65 - ዋና ዳይሬክተር
011- 276 32 80 - የሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት
E-mail-pfsa@ethionet.et
ፋክስ (Fax) 0112 75 25 55
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 21904

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
PHARMACEUTICALS FUND AND SUPPLY AGENCY (PFSA)
☎ 011-275 17 70, 011-276 06 76, 011-75 06 74 011-155 32 77, 011 275 25 55 ✉ 21904 E-mail: pfsa@ethionet.et

የመድኃኒቶች፤ የሕክምና ቁሳቁስና መሣሪያዎች የዋጋ አተማመን መመሪያ

356/2013

ሚያዝያ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

1. መግቢያ 2
2. ዓላማ 3
ክፍል አንድ 3
አጠቃላይ 3
3. አጭር ርዕስ 3
4. ትርጉም 3
5. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን 4
1. የዋጋ አወጣጥ እሴት (Values) 4
2. የዋጋ አተማመን መርሆዎች (costing Principles) 5
ክፍል ሁለት 5
6. ተግባርና ሃላፊነት 6
ክፍል ሶስት 6
7. ዋጋ ለማዉጣት የምንጠቀምባቸዉ ሰነዶች አያያዝ 6
8. በዋጋ ዉስጥ መካተት የሚገባቸዉ የወጪ አይነቶች (Cost elements) 7
8.1 የተገላባጭ ፈንድ 7
8.2 በተራድኦ ገንዘብ (በጤና ፕሮግራም) 8
9. የዋጋ አተማመን ሥርዓት 9
9.1 የተገላባጭ መድኃኒት ፈንድ (Revolving Drug Fund) ወይም መደበኛ 9
9.2 በተራድኦ ገንዘብ (በጤና ፕሮግራም) 10
ክፍል አራት 11
10. ግምታዊ የዋጋ አተማመን ሥርዓት 11
10.1 የባንክ አገልገሎት ክፍያ ሠነድ (Bank Servicie charge advice) ለወቅቱ ዋጋ ትመና 11
ያልቀረበ ከሆነ :- 11
10.2 የጉምሩክ ቀረጥ (Custom Duty Tax) ሠነድ ያልቀረበ ከሆነ 12
10.3 የመጓጓዣ ወጪ (Freight Charge) ሠነድ ያልቀረበ የሆነ 12
10.3.1. ጭነቱ በአየር ሲጓጓዝ 12
10.3.2. ጭነቱ በባህር ሲጓጓዝ 13
10.4 የመድን ሽፋን ወጪ (Insurance) ሠነድ ያልቀረበ የሆነ 14
ክፍል አምስት 15
11. በአቅርቦት ሂደት በሚከሰት ጉድለት ዋጋ አተማመን 15
11.1 ከመድን ድርጅት የሚሰበሰብ ጉድለት 15
11.2 ከአቅራቢ የሚሰበሰብ ጉድለት፣ 16
11.3 ከትራንስፖርት ድርጅት /አስረካቢ/ የሚሰበሰብ ጉድለት፡- 17
ክፍል ስድስት 17
12. የህዳግ እና የአገልግሎት ክፍያ አተማመን 17
12.1 የተገላባጭ ፈንድ መድሐኒቶች እና የሕክምና መገልገያዎች የአገልግሎት ክፍያ 17
12.2 የሕክምና መሳሪያዎች 18
12.3 የጤና ፕሮግራም መድሐኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች የግዢና የስርጭት አገልግሎት
ክፍያ 19
ክፍል ሰባት 19
13. ዋጋ ማስተካከያ ስለማድረግ 19
13.1. የመሸጫ ዋጋቸው ውድ የሆኑ መድኃኒቶች :- 19
13.2 የመክፈል አቅም የሌላቸው የህብረተሠብ ክፍሎች ለረጅም ጊዜ የሚወሠዱ መድሐኒቶች 20
13.3 ገበያን ለማረጋጋት የሚቀርቡ መድኃኒቶች፤ 20
13.4 የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተቃረቡ መድኃኒቶች፡- 20
14. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ 21
15. መመሪያዉን ስለማሻሻል 21

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency
Office of Board of Directors

የዋጋ አተማመን አፈፃፀም መመሪያ

የመድሐኒት ፈንድ እና አቅርቦት እጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 553/99 በተቋቋመዉና በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12 (2) እና 12 (11) የእጀንሲዉ ስራ አመራር ቦርድ የአፈፃፀም መመሪያዎችን ለማጽደቅና እጀንሲዉ የሚያስከፍለዉን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመወሰን በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህ የዋጋ አተማመን መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል።

1. መግቢያ

የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የተቋቀመበትን ዓላማ ለማሳካት የሕብረተሰቡን የመድኃኒት ፍላጐት ለማርካት፣ ጥራታቸውና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጡ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በቀጥታ ለጤና ተቋማት ለማድረስ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን በመሸፈን አቅርቦቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ዋጋዎችን ለመወሰን ይህንን መመሪያ ማዉጣት አስፈልጓል::

ኤጀንሲው የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እንዲወጣ የተገላባጭ መድኃኒት ፈንድ በመጠቀም በመንግሥት ጤና ተቋማት የሚፈለጉ መድኃኒቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የፈንድ ምንጩ ከመንግሥት ድጋፍ፣ ራሱ ከሚሰጠው አገልግሎት የሚገኝ የተጣራ ገቢ እንዲሁም ከልማት አጋሮች የሚገኙ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ መሠረት ያደረገ ነው::

ተገላባጭ መድኃኒት ፈንድ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል እና የሕብረተሰቡን የመድኃኒት ፍላጐት በዘለቄታነትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ትክክለኛ የፈንድ አጠቃቀምና ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ለተገዙት መድኃኒቶች በሁሉም የኤጀንሲው መሥሪያ ቤቶች ወጥ እና ትክክለኛ የዋጋ አተማመን ሥርዓት መተግበር አስፈልጓል:: በዚህ መመሪያ በተገላባጭ መድኃኒት ፈንድ እና በልማት አጋሮች ድጋፍ የሚገዙ መድኃኒቶች ሊያካትቱዋቸው የሚገቡ የዋጋ ዝርዝሮች (Cost elements) ለዋጋ አተማመን ሥራ በወቅቱ የማይደርሱ ሠነዶች ታሳቢ ያደረገ ግምታዊ የዋጋ አወጣጥ ስርዓት፣በጉዞ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የካሣ ተሰብሳቢ ሂሳብና የአገልግሎት ክፍያ የተካተተበት ነው:: የቀልጣፋ የዋጋ አወጣጥ ተግባራዊ በማድረግ በዴሊቨሪ ኖት የሚሰራጭበትን ሁኔታ በማስቀረት የግብአቶችን ስርጭት እንዲሳለጥ ለማድረግ፤ በሁሉም ቅርንጫፎች ለተቋማት የሚቀርቡ ግብዓቶች በአንድ አይነት ዋጋ ማቅረብ እንዲቻል፤ ይህ መመሪያ ወጥቷል::

2. ዓላማ

1. የተገላባጭ የመድሃኒት ፈንድ ወጪዉን ሽፍኖ ቀጣይነት እንዲኖረዉና ህብረተሰቡም በተመጣጣኝ ዋጋ መድሃኒት እንዲያገኝ ለማድረግ፣ እንዲቻል፣

2. የግብዓቶች ዋጋ እንደአስፈላጊነቱ ከማህበረሰቡ የመግዛት አቅም ጋር በማነጻጸር /cross subsidization/ ዉድ የሆነ ዋጋ ያለበትን የተወሰኑትን ክፍሎ አንስቶ ርካሽና ብዙ በሆኑት የሕክምና ቁሳቁሶችና መድኃኒቶች ላይ በማካካስ ገበያን እንዲረጋጋ ለማድረግ፣

3. ኤጀንሲዉ የሚያስከፍላቸዉ የአገልግሎት ክፍያዎች ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ሁሉንም ዓይነት ወጪዎችን የሚመልስና ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ለማድረግ፣

4. በሁሉም የኤጀንስው ቅርንጫፎች ለተቋማት የሚቀርቡ ግብዓቶች በአንድ አይነት ዋጋ ለማቅረብ እንዲቻል፣ ወጥ የሆነ አሠራርን ለመዘርጋት፣

5. በየደረጃው ያሉ ዋጋ ትመና ሥራ ሂደቶች ኃላፊነትና ተግባር ለመግለፅ

6. የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ አጭር የሆኑትን አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያስችል የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ ሃብት እንዳይባክን ለማድረግ፣

7. ለዋጋ ትመና የማይደርሱ ወጪዎች በቅድሚያ ግምታዊ (estimation) ዋጋ ዉስጥ ማካተትና ከትክክለኛዉ ወጪ ጋር በማገናዘብ ተገቢዉንና ወቅታዊ የሒሳብ ማስተካከያ ለማድረግ፣

ክፍል አንድ

አጠቃላይ

3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢፌድሪ የመድኃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ የዋጋ አተማመን መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
356/2013

4. ትርጉም

ሀ. ዋጋ ማለት አንድን ዕቃ ወይም አግልግሎት ለማምረትና ተጠቃሚዉ ድረስ ለማድረስ የሚዉጡትን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን ያካተተ የገንዘብ መጠን ማለት ነዉ፡፡

ለ. ተቋማት ማለት የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ማለት ነው

ሐ. ኤጀንሲ ማለት የመድሐኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ማለት ነው

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency Office of Board of Directors

መ. መድሐኒት ማለት ለሠው ሕክምና አገልግሎት የሚውሉ መድሐኒቶችን፤ ኬሚካሎችን፤ ቁሳቁሶችን ማለት ነው

ሠ. የተገላባጭ መድሐኒት ፈንድ ማለት በኤጀንሲው ውስጥ የሚንቀሳቀስ መደበኛ የመድሐኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች በጀት ለማመልከት ነው

ረ. የጤና ፕሮግራም ማለት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተራድኦ ድጋፍ የሚገኙ የመድሐኒቶችና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥና ስርጭት በጀት ለማመልከት ነው

ሰ. የልማት አጋር ማለት ለጤና ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚሰጥ ድርጅት ወይም ተቋም ማለት ነው

ሸ. ቀጥተኛ ወጪ ማለት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወደ ተጠቃሚዎች ለማድረስ የሚወጡና ለዕቃው/አገልግሎቱ ብቻ ተለይተው የሚወጡ ወጪን ሲያመለክት የመግዣ ዋጋ፤ ማጓጓዣ፤ የባንክ አገልግሎት፤ የመድን ዋስትና ሽፋን፤ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል

ሸ. ቀጥተኛ ያልሆነ ወጪ ማለት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወደ ተጠቃሚዎች ለማድረስ የሚወጡና ለዕቃው/አገልግሎቱ በጋራ የሚወጡና በድርሻ የሚደለደሉ ወጪን ሲያመለክት የመጋዘን፤ የትራንዚት፤ የማስፈተሸ፤ የጫኝና አውራጅ፤ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል

በ. ቋት ማለት የሒሳብ መደብ ወይም አካውንት ማለት ነው፡፡

5. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በዋናዉ መሰሪያ እና በሁሉም ቅርንጫፎች በስራ ለይ ይውላል

1. የዋጋ አወጣጥ እሴት (Values)

ሀ. በአገርቱ ውስጥ ለሁሉም ተጠቃሚ በፍትሀዊነት ማድረስ (Eqiuty)

ለ. ሁሉም ተጠቃሚ/ታካሚ ሊያገኘው የሚችል ማድረግ (Affordability)

ሐ. ብክነትን፡ ብልሽትንና የመሳሰሉትን በመቀነስ ወጪን መቆጣጠር (economy)

መ. ወጪን መሸፈን (Cost Recovery)

ሠ.የሚፈለገውን ያህል በተፈለገ ቦታና ጊዜ እንድደርስ ማድረግ (efficiency)

2. *የዋጋ አተማመን መርሆዎች (costing Principles)*

ሀ. በኤጀንሲዉ ወጥ የሆነ የመድሃኒት ዋጋ አተማመን ስርዓት ለመዘርጋት፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መርሆችን ይከተላል፡

ለ. የአንድ ዕቃ ወይም ግልጋሎት የዋጋ ተመን ሊያካትታቸዉ የሚገቡ መሰረታዊ ወጪዎች ተመሳሳይ ቢሆንም፤ተቋማት ለህብረተሰብ እንደሚሰጡት አገልግሎት እና በተቋቋሙበት ሁኔታ በተለያዩ መንገዶች የዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ መተመን ይችላሉ፡፡

ሐ. በዋጋ ዉስጥ የሚካተቱ ወጪዎች በአብዛኛዉ ለእያንዳንዱ ዕቃ በተናጠል ቢሆኑም በጥቅል ለሚገዙ ዕቃዎች ወጪዎቻቸዉን ተቋማት የሥራ ባህሪያቸዉ መሰረት በማድረግ የዋጋ አተማመን ስልታቸዉን መቀየስ፡፡

መ. ኤጀንሲው የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ እና በመላው አገሪቱ የመድሃኒት ዋጋ ተመሳሳይ እንዲሆንና በዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው ወጪዎች በአግባቡ እንዲካተቱ ማድረግ ከውጭ ሀገር ተገዝተው ለሚገቡ መድኃኒቶች በዋናው መሥሪያ ቤት በፈንድ አስተደደር ዳይሬክቶሬት ሲሆን፣ የሀገር ውስጥ መድኃኒቶች ግን በዋናው መሥሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ የፈንድ አስተዳደር ክፍል ማከናወን ፡፡

ሠ. የሁሉም ቅርንጫፎች የሚያቀርቡበት ዋጋ በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ተጠቃሚዎች በተመሳሳይ ዋጋ እንዲያገኙ የማድረግ አላማን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ቅርንጫፎች የተለየ የዋጋ መተመን ስራ እንዳያከነናዉኑ ማድረግ፡፡

ረ. ከኢንሹራንስ ጋር በተያያዘ እና ከዋናዉ መስሪያ ቤት ወደ ቅርንጫፍ፣ ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ እና ከቅርንጫፍ ወደ ዋናዉ መስሪያ ቤት ክምችት ሲተላለፍ የሚኖረዉን የኢንሹራንስና የመጓጓዣ ተጨማሪ ወጪ በወጪ እንዲመዘገብ ለማድረግ፡፡

ሰ. መድኃኒቶች ከመጋዘን በመጠቀሚያ ጊዜያቸው ቅደም ተከተል የሚሠራጩ ቢሆንም፣ ለቁጥጥር ቀላልነት እና ለአሠራር የሚያመች የዋጋ አወጣጥ ሥርዓት ተለዋዋጭ ማዕከላዊ ዋጋ (Moving Average Cost) ይሆናል፡፡ ይህ ተለዋዋጭ ማዕከላዊ ዋጋ ተግባራዊ የሚሆነው መድኃኒቶቹ በሂሳብ ቋት (Account)፣ በስም (Description) ፣ በመለኪያ (Unit) እና በአምራች (Manufacturer) ተመሳሳይ ሆነው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

6. ተግባርና ሃላፊነት

1. የዋጋ ሂሳብ ሰራተኛ (Cost accountants) ፦ይህ ዋናው የሥራ ሂደት ሲሆን ተግባሩም መረጃ ሰነዶችን /ዳታ መሰብሰብ፤ መመዝገብ፤ መከፋፈል፤ ማመዛዘን፤ ማጠቃለል እና የተለያዩ ዶክመንቶችን በማገላበጥ ትክክለኛውን ዋጋ መተመንና ማጥራት ነዉ።

2. ከፍተኛ የዋጋ ሂሳብ ሰራተኛ (Senior cost accountant) ፦ ብዙ ሃላፊነት ያለበት ተዛማጅ የሆኑ የሂሳብ መግለጫ የማቅረብ ፤ ዋጋዎችን የማገናዘብ እና ትክክለኘነት የማረጋገጥ ስራ የሚሰራ ነዉ። በአጠቃላይ ከፍተኛ ሂሳብ ሰራተኛ ማለት ጥልቅ የሆነ የዋጋ ግንዛቤ ያለዉ እና ግንዛቤዉን በትክክለኛዉ መንገድ ለእጀንሲዉ የሚሰጥ እና በኤጀንሲዉ የመረጃ ቋት እንዲመዘገብ የሚያደርግ ነዉ ፡፡

ዋና ዋና ስራዎቹም፡

ሀ. ወርሃዊ የዋጋ መግለጫ መስጠት

ለ. የዋጋ አሰራሮችን በየጊዜዉ እንዲሻሻሉ አስተዋጾ ማድረግ

ሐ. ለከፍተኛ ሃላፊዉ ወርሃዊ የክምችት እና ሥርጭት እንዲሁም በመጋዘን ያለ ክምችት የታረቀበትን ሪፖርት የማቅረብ

ክፍል ሶስት

7. ዋጋ ለማዉጣት የምንጠቀምባቸዉ ሰነዶች አያያዝ

ሀ. ከውጭ ሀገር ለሚገዙ መድኃኒቶች ክፍያቸው በቅድሚያ ስለሚከፈል የተከፈለውን ሂሣብ ለመቆጣጠር በጉዞ ላይ ያለ ክምችት /Goods in Transit/ በሚል እና በስሩ በሚከፈቱ በተለያዩ የሂሣብ ቋቶች ተከፍተው በየግዥ ትዕዛዙ ተለይተው ይመዘገባሉ፡፡

ለ. ከግዢ ጋር የተገናኙ የቀጥተኛ ወጪ ማስረጃዎች፤ የማጓጓዣ፣ ከወደብ እስከ መጋዘን ያሉ ወጪዎች፣ የኢንሹራንስ. ወዘተ ሰነዶች ተለይተዉ ይያያዛሉ፡፡

ሐ. ቅርንጫፍ የመጓጓዣ ወጪዎች ማለትም የነዳጅ፣ የውሎ አበልና የመድን ሽፋን ወጪ. ወዘተ በዋጋ የሚካተት ቢሆንም የነዚህ ወጪዎች በቅድሚያ ታውቀው ለዋጋ ትመና ስለማይደርሱ ወጪዎቹ በወጪነት ተመዝግበዉ ይያዛሉ፡፡ ለዋጋ ተመና አገልግሎት እነዚህ ወጪዎች በጥቅል ድርሻ ተወስኖ በዋጋው ላይ በመቶኛ ታስቦ ይሰላል፤፤

መ. ያለፉት ጊዜያቶችን ወጪዎች ግምት ዉስጥ በማስገባት የተወሰነ ግምታዊ መጠን በቀጥታ ዋጋው ላይ እንዲጨመር ስለሚደረግ መረጃዎች ተጠናቅረው እንዲመዘገቡ ያደርጋል፡፡

8. በዋጋ ዉስጥ መካተት የሚገባቸዉ የወጪ አይነቶች (Cost elements)

8.1 የተገላባጭ ፈንድ

8.1.1 የዉጭ ሀገር ግዢዎች

በዚህ የግዢ ዓይነት ስር የሚካተቱ የዋጋ ወጪዎች ፡-

1.ቀጥተኛ ወጪዎች

ሀ. የመድሃኒቱ የአቅራቢው ዋጋ (Invoice / FOB Value)

ለ. በጉዞ ላይ መድን ዋስትና ሽፋን የተከፈለ ዋጋ (Insurance cost)

ሐ. ጭነቱ እስከ ማዕከላዊ መጋዘን ለመጓጓዣ የተከፈለ ወጪ (Air or sea Freight and inland transport from Djibuti to Dry port)

መ. የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ (Import tax) ይሸፈናል

ሠ. የተከላና የስልጠና ወጪዎች እንደአስፈላጊነቱ (Installation and training cost)

ረ. የባንክ አገልግሎት ክፍያ (Bank Service charge) ይሆናሉ፡፡

2. ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች

ሀ. መጫኛ እና ማዉረጃ

ለ. የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የአየር መንገድ እና የመጋዘን ኪራይ

ሐ. ከሞጆ ወይም ከአየር መንገድ እስከ ማዕከላዊ መጋዘን የሚጓጓዝበት የትራንስፖርት ዋጋ

መ. የፍተሻ አገልገሎት ክፍያ(FMHCA) እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች

ሠ. የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች

ረ. የቢሮ መገልገያዎች፡ የፅሕፈት መሣሪያዎች፤ ስልክ፡ ወሃ፤ ማብራት፤ ወዘተ.. ወጪዎች

ሰ. የዋጋ ግሽበት፡ ወለድ፡ የባንክ አገልግሎት ወዘተ

3. ወደ ቅርንጫፎች ሲሰራጭ

ሀ. ትራንስፖርት

ለ. ኢንሹራንስ

ሐ. ጫኚ እና አዉራጅ

መ. መጋዘን ኪራይና ጥገና

ሠ. የቅርንጫፍ ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች

ረ. የቢሮ መገልገያዎች፡ የፅሕፈት መሣሪያዎች፤ ስልክ፡ ወሃ፤ ማብራት፤ ወዘተ.. ወጪዎች

ሰ. የዋጋ ግሽበት፡ ወለድ፡ የባንክ አገልግሎት ወዘተ

8.1.2 የሀገር ዉስጥ ግዢዎች

ከአገር ዉስጥ አቅራቢዎች ለተገዙ መድሃኒቶች በተገባዉ ዉል እና በአቅራቢዉ ኢንቮይስ ዋጋ መሰረት ይሆናል፤፤

8.2 በተራድኦ ገንዘብ (በጤና ፕሮግራም)

8.2.1 የዉጭ ሀገር ግዢዎች

በዚህ የግዢ ዓይነት ስር የሚካተቱ የዋጋ ወጪዎች

1. ቀጥተኛ ወጪዎች

ሀ. የመድሃኒቱ ዋጋ (FOB Value)

ለ. ለመድን ዋስትና ሽፋን የተከፈለ ዋጋ (Insurance cost)

ሐ. ለመጓጓዣ የተከፈለ ወጪ (Air or sea and inland Freight cost)

መ. የተካላና የስልጠና ወጪዎች እንደሁኔታው (Installation and training cost)

ሠ. የባንክ አገልግሎት ክፍያ (Bank Service charge) ናቸዉ፡፡

ረ. የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ እንደአስፈላጊነቱ (Import tax) ይሸፈናል (በበጀት የሚሸፈን)

2. ከዚህ በታች ያሉትን ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች በጥቅል ድርሻ ተወስኖ በዋጋው ላይ በመቶኛ ታስቦ ይሰላል፤

ሀ. መጫኛ እና ማዉረጃ

ለ. የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የአየር መንገድ እና የመጋዘን ኪራይ

ሐ. ከሞጆ ወይም ከአየር መንገድ እስከ ማዕከላዊ መጋዘን የሚጓጓዝበት የትራንስፖርት ዋጋ

መ. የፍተሻ አገልገሎት ክፍያ (FMHCA) እና ሊሎች ተያያዥ ወጪዎች

ሠ. የቢሮ መገልገያዎች፡ የፅሕፈት መሣሪያዎች፤ ስልክ፡ ወሃ፤ ማብራት፤ ወዘተ.. ወጪዎች

ረ. የዋጋ ግሽበት፡ ወለድ፡ የባንክ አገልግሎት ፡፡ የብልሽት ማካካሻ ወዘተ

8.2.2 የሀገር ዉስጥ ግዢዎች

ከአገር ዉስጥ አቅራቢዎች ለተገዙ መድሃኒቶች በተገባዉ ዉል መሰረት በአቅራቢዉ ኢንቮይስ ዋጋ መሰረት ይሆናል፡፡

8.3 በእርዳታ የተገኘ መድኃኒት

ለጤና ፕሮግራም የሚዉሉ መድሃኒቶች በዕርዳታ ሲገኝ የመድሃኒቱ ዋጋ የሚሆንዉ የአቅራቢዉ ኢንቮይስ ዋጋ ሲሆን የመድሃኒቱ ኢንቮይስ ላይ ዋጋ ከሌለዉ በክምችት ላይ ያለዉን ተመሳሳዩን መድሃኒት ዋጋ የሚወስድ ይሆናል፡፡ በክምችት ተመሳሳይ መድሃኒት በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተር በሚሰየሙ ባለሙያዎች ተጠንቶ ዋጋ ይተከላል፡፡

8.4 ከመደበኛ ወደ ፕሮግራም ሽያጭ ለማከናወን አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የግዢና የስርጭት አገልግሎት ክፍያዉ ህዳግ (Markup) ሳይጨምር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

8.5 ከፕሮግራም ወደ መደበኛ

ከፐሮግራም በውሰት የተላለፈዉን ክምችት ዋጋ መደበኛዉን ዋጋ አተማመን እና ወጪ ምለሣ ማካካሻን ስርአትን ተከትሎ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

9. የዋጋ አተማመን ሥርዓት

9.1 የተገላባጭ መድኃኒት ፈንድ (Revolving Drug Fund) ወይም መደበኛ

ሀ. የዉጭ ሀገር ግዢዎች ዋጋ አተማመን

1. ከአገር ዉጭ ለተገዙ መድሃኒቶች የዋጋ አተማማን በዉጭ ምንዛሪ ያሉትን ዋጋዎች ዕቃው በገባበት ቀን ባለዉ የዉጭ የምንዛሪ ተመን በመጠቀም ወደ ብር ይለወጣል፡፡ ሁሉም መካተት የሚገባቸዉ ወጪዎች የመድሃኒቱ ዋጋ' ለመድን ዋስትና ሽፋን የተከፈለ ዋጋ ለመጓጓዣ የተከፈለ ወጪ የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ የባንክ አገልግሎት ክፍያ እንዲሁም 11 በመቶ ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ማካካሻ/ መመለሻ በመደመር አጠቃላይ የመድሃኒቱ የመግዣ ዋጋ (landed cost/ GRV value) ይሆናል፡፡

10. አጠቃላይ የመድሃኒቱ የመግዣ ዋጋ (landed cost) ለተገዛዉ መድሃኒት ብዛት በማካፈል የአንዱን መድሃኒት ነጠላ ዋጋ ይተመናል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency Office of Board of Directors

11. የገባዉ መድሃኒት ጉድለት ወይም ያልገባ መጠን ካለዉ (Damage or missing) የጉድለቱ ወይም ያልገባዉ መድሃኒት ዋጋ ተሰልቶ ከሚመለከተዉ የመድን ድርጅት ወይም አቅራቢ ወይም አጓጓዥ ድርጅት እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

ለ. ሀገር ዉስጥ ግዢዎች ዋጋ አተማመን ሥርዓት

12. ከአገር ዉስጥ አቅራቢዎች ለተገዙ መድሃኒቶች ኤጀንሲዉ በገባዉ ዉል መሰረት በአቅራቢዉ ኢንቮይስ ዋጋ የሚተመን ይሆናል፡፡

9.2 በተራድኦ ገንዘብ (በጤና ፕሮግራም)

ሀ. የዉጭ ሀገር ግዢዎች ዋጋ አተማመን ሥርዓት

13. ከአገር ዉጭ ለተገዙ መድሃኒቶች የዋጋ አተማማን በዉጭ ምንዛሪ ያሉትን ዋጋዎች በባንክ debit advice ባለዉ የዉጭ የምንዛሪ ተመን በመጠቀም ወደ ብር ይለወጣል፡፡ ሁሉም መካተት የሚገባቸዉ ወጪዎች የመድሃኒቱ ዋጋ፣ ለመድን ዋስትና ሽፋን የተከፈለ ዋጋ፤ ለመጓጓዣ የተከፈለ ወጪ፤ የባንክ አገልግሎት ክፍያ፤ እንዲሁም 11 በመቶ ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች መመለሻ በመደመር አጠቃላይ የመድሃኒቱ የመግዣ ዋጋ (total landed cost) ይሆናል፡፡

14. አጠቃላይ የመድሃኒቱ የመግዣ ዋጋ (landed cost) ለተገዛዉ መድሃኒት ብዛት በማካፈል የአንዱን መድሃኒት ነጠላ ዋጋ ይተመናል፡፡

15. የገባዉ መድሃኒት ጉድለት ወይም ያልገባ መጠን ካለዉ (Damage or missing) የጉድለቱ ወይም ያልገባዉ መድሃኒት ዋጋ ተሰልቶ ከሚመለከተዉ የመድን ድርጅት ወይም አቅራቢ ድርጅት በግዥ ዳይሬክቶሬት በኩል እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

ለ. ሀገር ዉስጥ ግዢዎች ዋጋ አተማመን ሥርዓት

16. ከአገር ዉስጥ አቅራቢዎች ለተገዙ መድሃኒቶች ኤጀንሲዉ በገባዉ ዉል መሰረት በአቅራቢዉ ኢንቮይስ ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

ሐ - የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ (office Supplies) ቋሚ ዕቃዎች ፤ ተሽከርካሪዎች (Fixed Asset)

9. በሥጦታ የተገኙ ቋሚ ዕቃዎች (Donated Assets) በአገሪቱ የመንግሥት ዕቃ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ፤ በሂሳብ ህጎችና፤ እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መመሪያዎችና ደንቦች መሠረት የሚተመን

ይሆናል፤፤

ክፍል አራት

10. ግምታዊ የዋጋ አተማመን ሥርዓት

መድኃኒት ለሕብረተሰቡ ጤና ከሚሰጠው የጐላ ድርሻ በመነሳት በኤጀንሲው ተገዝተው የሚቀርቡ የተገላባጭ ፈንድ እና የጤና ፕሮግራም መድሐኒቶች በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች ለዋጋ አተማመን የሚረዱ ሠነዶች ተሟልተው በማይገኙበት ወቅት እና መድሐኒቶቹ በአስቸኳይ ለሥርጭት በሚፈለጉበት ጊዜ የመድሃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት በጽሁፍ ሲጠይቅ የመድሐኒቱ ዋጋ በግምት እንዲተመን ይደረጋል፡፡

10.1 የባንክ አገልገሎት ክፍያ ሠነድ (Bank Servicie charge advice) ለወቅቱ ዋጋ ትመና ያልቀረበ ከሆነ ፡-

1. የግዥ ትዕዛዙ ክፍያ CAD ሲሆን ፡-
   - በወቅቱ በሚኖረው የባንክ አገልግሎት ክፍያ ታሣቢ በማድረግ የኢንቮይሱ የዉጭ ምንዛሪ ዋጋ ክፍያው ከባንክ በተቀነሰበት ቀን፤ በደረሰኙ ቀን፤ ክምችቱ ገቢ በተደረገበት ዕለት በቅደም ተከተላቸው ባሉት የዉጭ ምንዛሪ ተመን ወደ ብር በመቀየር በተገኘዉ የብር ዋጋ ላይ 2% የባንክ አገልግሎት ክፍያው ይሰላል፡፡ ሆኖም ለሌሎች በቅድሚያ ሊተመኑ የማይችሉ ተዛማጅ ወጪዎች (photocopy charge, cable charge) መሸፈኛ እንዲሆን በተሰላዉ የባንክ አገልግሎት ተመን ዋጋ ላይ 1% ተጨምሮ ዋጋ ውስጥ ይካተታል፡፡

2 የግዥ ትዕዛዙ ክፍያ Letter of credit ሲሆን፡-

ሀ. በወቅቱ በሚኖረው የባንክ አገልግሎት ክፍያ ታሣቢ በማድረግ የኢንቮይሱ የዉጭ ምንዛሪ ክፍያው ከባንክ በተቀነሰበት ቀን፤ በደረሰኙ ቀን፤ ክምችቱ ገቢ በተደረገበት ዕለት በቅደምተከተላቸው ባሉት የዉጭ ምንዛሪ ተመን ወደ ብር በመቀየር በተገኘዉ የብር ዋጋ ላይ 1.5% የባንክ አገልግሎት ክፍያው ይሰላል፡፡ ሆኖም ለሌሎች በቅድሚያ ሊተመኑ የማይችሉ ተዛማጅ ወጪዎች (photocopy charge, cable charge, Crosspondance fee) መሸፈኛ እንዲሆን በተሰላዉ የባንክ አገልግሎት ተመን ዋጋ ላይ 2% ተጨምሮ ዋጋ ውስጥ ይካተታል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency Office of Board of Directors

ለ. ለግዥ ትዕዛዙ ማስተካከያ /የሌተር ኦፍ ክሬዲት LC Amendement/ ማስተካከያ የሚወጣው

ወጪ በሚመለከተው ኃላፊ ሲፈቀድና ከባንክ ሂሣብ ቋት መቀነሱ ሲረጋገጥ በወጪ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

10.2 የጉምሩክ ቀረጥ (Custom Duty Tax) ሠነድ ያልቀረበ ከሆነ

የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ ሰነድ በተለያዩ ምክንያቶች ለዋጋ ትመና በወቅቱ ያልቀረበ ከሆነ የገባዉን መድሃኒት ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ወጪዎች በማከል ግምታዊ ዋጋ እንዲተመን ይደረጋል፡፡

ሀ. የኢንቮይስ ዋጋ ዕቃው በገባበት ቀን መሰረት ወደ ብር በመለወጥ ፣ ለመድን ዋስትና ሽፋን የተከፈለ ወጪ እንዲሁም ለመጓጓዣ የተከፈለ ወጪ 1/3ኛዉን በመወሰድ ወጪዎች በመደመር በወቅቱ የጉምሩክ ታሪፍ መሰረት (ለመድሃኒት የጠቅላላ ዋጋዉ 5%) ተደርጎ ግምታዊ ዋጋ ይሰላል፡፡ ሆኖም በዉጭ ምንዛሪ ተመን ለዉጥ (Exchange rate difference) ምክንያት የሚፈጠር ልዩነት ለማጥበብ በተሰላዉ የጉምሩክ አገልግሎት ተመን ዋጋ ላይ 2% ተጨምሮ ዋጋ ውስጥ ይካተታል፡፡

10.3 የመጓጓዣ ወጪ (Freight Charge) ሠነድ ያልቀረበ የሆነ

የመጓጓዣ ወጪ የሚተመነዉ በዋናነት የጭነቱ ክብደትና ባህርይ ክምችቱ መሰርት ተደርጎ መሆኑን ለግምታዊ ዋጋ በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ካለዉ የስራ ጠባይና ልምድ /trend መሰረት በማድረግ ጭነቱ ለስርጭት በአስቸካይ ሲፈለግና ከአጓጓዡ የመጓጓዣ ወጪዉ ለማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን በሚከተለዉ መንገድ ግምታዊ የጭነት ዋጋ እንዲተመን ይደረጋል፡፡

10.3.1.ጭነቱ በአየር ሲጓጓዝ

ሀ/ ክምችቱ የታዘዘዉ በአየር እንዲጓጓዝ ሆኖ በቅድሚያ ክፍያዉ የተተመነለት ከሆነ የተተመነዉ የጭነት ዋጋ በባንክ ደረሰኙ ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት በብር ተለዉጦ ዋጋ እንዲተመን ይደረጋል፡፡ ዋናዉ የጭነት ደረሰኝ ሲገኝ ዋጋው ከበዛ ወይም ካነሰ በወጪ ወይም በልዩ ገቢ እንደቅደም ተከተሉ ይመዘገባል፡፡

ለ/ የታዘዘዉ ክምችት በአየር ሆኖ የጭነቱ ዋጋ በቅድሚያ ያልተተመነ ከሆነ ነገር ግን የአየር ማጓጓዣ ሰነድ (Air way bill) ያለዉ ሲሆን በሰነዱ የተቀመጠዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን ክምችቱ ገቢ በተደረገበት ቀን ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን በማስላት ወደ ብር ተለዉጦ ግምታዊ ወጪ ይተመናል፡፡ ሆኖም በዉጭ ምንዛሪ ተመን ለዉጥ (Exchange rate difference) ና ተዛማጅ ወጪዎች ምክንያት የሚፈጠር ልዩነት ለማጥበብ በተሰላዉ የጉምሩክ አገልግሎት ተመን ዋጋ ላይ 2% ተጨምሮ ዋጋ ውስጥ ይካተታል፡፡

ሐ/ የታዘዘዉ ክምችት በአየር ሆኖ የጭነቱ ዋጋ በቅድሚያ ያልተተመነ ከሆነ እንዲሁም የአየር ማጓጓዣ ሰነድ (Air way bill) ወይም የጉምሩክ ተመን ከሌለዉ በአየር የሚመጡ ክምችቶች ማጓጓዣ ዉድ መሆኑን ግምት ዉስጥ በማስገባት ምንም ሰነድ ባልተሟላበት ሁኔታ ባነሰ ዋጋ እንዳይቀርብ የሚያጋጥመዉን ስጋት ለመቀነስ የኢንቮይሱ የዉጭ ምንዛሪ ዋጋ በባንክ ደረሰኝ ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን ወደ ብር በመቀየር በተገኘዉ ስሌት 15% በማስላት የጭነት ግምታዊ ወጪ ይተመናል፡፡

10.3.2.ጭነቱ በባህር ሲጓጓዝ

ሀ/ ክምችት በባህር የተጫነ ሆኖ ዋጋዉ በቅድሚያ ያልተተመነ ከሆነ ነገር ግን የባህር ማጓጓዣ ሰነድ (Bill of lading) ያለዉ ሲሆን፤ በሰነዱ የተቀመጠዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን ክምችቱ ገቢ በተደረገበት ቀን ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን በማስላት ወደ ብር ተለዉጦ ግምታዊ ወጪ ይተመናል፡፡ ሆኖም በዉጭ ምንዛሪ ተመን ለዉጥ (Exchange rate difference) ና የአገልግሎት ወጪዎች ምክንያት የሚፈጠር ልዩነት ለማጥበብ በተሰላዉ የጉምሩክ አገልግሎት ተመን ዋጋ ላይ 4.5% ተጨምሮ ዋጋ ውስጥ ይካተታል፡፡

ጭነቱ በመልቲ ሞዳል (Multi modal) ሆኖ የአገር ዉስጥ መጓጓዣ ወጪ ካልታወቀ የኢንቮይሱ ዋጋ ክምችቱ ገቢ በተደረገበት ቀን ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን በማስላት ወደ ብር ተለዉጦ የዚሁ ስሌት 4.5% ግምታዊ ወጪ ይተመናል፡፡

ለ/ የታዘዘዉ ክምችት በባህር ሆኖ የጭነቱ ዋጋ በቅድሚያ ያልተተመነ ከሆነ እንዲሁም የባህር ማጓጓዣ ሰነድ (Bill of lading) ከሌለዉ የኢንቮይሱ የዉጭ ምንዛሪ ዋጋ በባንክ ደረሰኝ ባለዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን ወደ ብር በመቀየር በተገኘዉ ስሌት 4.5% በማስላት የጭነት ግምታዊ ወጪ ይተመናል፡፡

10.4 የመድን ሽፋን ወጪ (Insurance) ሠነድ ያልቀረበ የሆነ

በግዥ ሂደት የነበረው ትዕዛዝ የገቢ ሠነድ ተቆርጦለት ነገር ግን የመድን ዋስትና ሽፋን ወጪ በወቅቱ ያልቀረበ ከሆነ ግምታዊ ዋጋ እንዲተመንለት ይደረጋል፡፡ ግምታዊ ዋጋው በግዥ ትዕዛዙ ላይ ያለዉን የዉጭ ምንዛሪ ከባንክ በተቀነሰበት ቀን፣ በደረሰኙ ቀን፣ ክምችቱ ገቢ በተደረገበት ዕለት በቅደምተከተላቸው ባሉት የምንዛሪ ተመን በመጠቀም ወደ ብር እንዲለወጥ በማድረግና በዋጋዉ ላይ የማጓጓዣ 10% በመጨመር የመድን ዋስትና ሰጪው የወቅቱን የማባዣ ተመን (1%) በመጠቀም የሚሰላ ይሆናል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency
Office of Board of Directors

ክፍል አምስት

11. በአቅርቦት ሂደት በሚከሰት ጉድለት ዋጋ አተማመን

በአቅርቦት ሂደት ወቅት ኤጀንሲዉ ሊያገኘዉ የሚገባውን ንብረት ካላገኘ ምክንያቱን በማጣራት የስምምነት ውሉን መሰረት በማድረግ ለጉድለቱ ተጠያቂ የሚሆን አካል በመለየት እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

11.1 ከመድን ድርጅት የሚሰበሰብ ጉድለት

ሀ/ በግዥ ሂደት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ከአቅራቢው መጫናቸው ተረጋግጦ ሆኖም በመንገድ ላይ የጠፋ፣ የተበላሹ ወይም የጐደሉ መድኃኒቶች በአግባቡ ማጣሪያ ተደርጐ በ "incoterm"መሰረት በመድን ድርጅት መመሪያ /ውሉ ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ግዥ ዳይሬክቶሬት በኩል የጉድለት ካሣ (Claim notification) ተሞልቶና ለመድን ድርጅቱ እንዲደርስ ተደርጐ ኮፒው ከገቢ ሠነዱ (GRNF) ጋር መያያዝ ይኖርበታል፣

ለ/ በክምችት ገቢ ሠነድ (GRNF, GRV) ላይ በጉድለት ወይም በመበላሸት የተመዘገቡ መድኃኒቶች የጉድለት ካሣ ማሳወቂያ (Claim Notification) የተሞላለት መሆኑን በማረጋገጥ በመድኃኒቱ የግዥ ትዕዛዝ ዋጋ ላይ 10% በመጨመር የስምምነት ውሉን በማጤን በመድን ድርጅቱ ወይም በአቅራቢው ስም በተሰብሳቢነት እንዲያዝ ይደረጋል፣

ሐ/ ጉድለቱ ወይም የተበላሸው መድኃኒት ዋጋ በአንድ ግዥ ትዕዛዝ ከብር 300.00 /ሦስት መቶ ብር/ የማይበልጥ ከሆነ ዋጋውን ለማስመለስ የሚደረገው ጥረት ከሚሰበሰበው ብር ጋር ስለማይመጣጠን በወጪነት እንዲያዝ ይደረጋል፣

መ/ ከመድን ድርጅት ለሚሰበሰብ ሂሳብ የመጠየቂያ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመድሃኒትና የሕ/መገልገያዎች ግገር ዳይሬክቶሬት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ የመድን ተሰብሳቢ ሂሳብ

የተጠየቀበት (claim notification) ከክምችት ገቢ ሰነድ (GRNF) ጋር ተያይዞ ለፈንድ አስተዳደር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ ከመድን ድርጅት ገንዘቡን የማሰባሰብ ስራ በፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ክትትል ተደርጎ ገቢ ይደረጋል፤

11.2 ከአቅራቢ የሚሰበሰብ ጉድለት፣

በግዥ ትዕዛዙ የተጠቀሰው ብዛት በአቅራቢው ምክንያት ሳይላክ ከቀረ፣ ተልኮም ጥራቱን ያላሟላ መድሐኒት ከሆነ ከአቅራቢው እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡

ሀ. ሳይላክ የቀረ ክምችት (short landed)

በግዥ ትዕዛዙ መሠረት የተጠቀሰውን ያህል ብዛት በአቅራቢው ኢንቮይስ ተጠቅሶ በመንገድ ወረቀት (Way bill) አለመጫኑ ሲረጋገጥና እና በክምችት ገቢ ሠነድ ያልተቆረጠለት መሆኑ ተረጋግጦ በጉድለት የገባ ተብሎ በመድሃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት ሲቀርብ፣ አቅራቢው እንዲሸፍን በመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ግዥ ዳይሬክቶሬት ተጠይቆ እንደሚሸፍን ሲረጋገጥ በግዥ ትዕዛዙ ላይ ያለውን ዋጋ በመጠቀም ጉድለቱ ተሰልቶ ድርጅቱ ካስያዘዉ የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ወይም ከቀሪ ክፍያ ላይ በመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች ግዢ ዳይሬክቶሬት ጥያቄ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ ጉድለቱ ከተያዘው ገንዘብ በላይ ከሆነ በህግ ወይም በድርጅቱ ስም ተመዝግቦ የሚመለከተው ኢንሹራንስ ኩባኒያ እንዲያውቀውና እንዲከታተለው ይደረጋል፡፡

ይህም ጉድለት በሚተካበት ጊዜ ክምችቱ ገቢ ተደርጎ ከአቅራቢው የተያዘው ሂሳብ አንጻር የሚመዘገብ ይሆናል፤፤

ለ. የጥራት ጉድለት ያለበት ክምችት

ከአቅራቢው የተላኩ መድኃኒቶች በሙሉም ሆነ በከፊል በተለያዩ ምክንያቶች የተቀመጠላቸው መሥፈርቶች ያላሟሉ ሆነው ሲገኙ አቅራቢውን እንዲከፍል በውሉ መሰረት ለግዥ ትዕዛዙ የወጡ ወጪዎች በተሰብሳቢነት ይያዛል፤ ወጪዎቹም የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፡-የመግገና ዋጋ (Landed cost)፤ ለትራንስፖርት፤ ኢንሹራንስ፤ ቀረጥና የመሳሰሉትን ወጪዎች ጨምሮ በማስላት በተሰብሳቢ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency — Office of Board of Directors

ሆኖም ወጪዉ ከብር 300.00 /ሦስት መቶ ብር/ በታች የሆነ ከውጭ አቅራቢ የሚሰበሰብ ጉድለት ከአቅራቢዎች ለመሰብሰብ የሚደረገው ወጪ እና ጊዜ ከሚገኘው ገንዘብ በላይ ስለሚሆን በወጪነት መመዝገብ ይቻላል፡፡

11.3 ከትራንስፖርት ድርጅት /አስረካቢ/ የሚሰበሰብ ጉድለት፡-

ከወደብ ወደ ዋናው መ/ቤት ወይም ከዋናው መ/ቤት ወደ ቅርንጫፍ መጋዘን በጭነት ተሽከርካሪ ሲጓጓዝ የመድኃኒት ጉድለት መድረሱ በክምችትና ሥርጭት ዳይሬክቶሬት ከተረጋገጠ ጉድለቱን ያደረሰዉ አካል ፤ አጓጓዥ ድርጅት ወይም ሾፌሩ በመድኃኒቱ ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ እስከሚከፍል በተሰብሳቢነት ይያዛል፡፡

ክፍል ስድስት

12. የህዳግ እና የአገልግሎት ክፍያ አተማመን

ኤጀንሲዉ በአዋጅ ከተደነገገለት የፈንድ ምንጭ ዘዴዎች አንዱና ዋነኛዉ ከአገልግሎቱ የሚያገኘዉ የተጣራ ገቢ መሆኑና ይህንኑ በማቆቆሚያ አዋጅ ቁጥር 553/99 አንቀፅ 12(11) በተፈቀደለት መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ተመን የህብረተሰቡ የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሁም የግገር፣ የክምችት፣ የመጋዘን ስርጭት፤ የተሽከርካሪ ጥገና፣ የአሰተዳደር እና የመሳሰሉትን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን ለመሸፈንና የመሠረታዊ መድሐኒቶች አቅርቦቱን በተመጣጣኝ ዋጋ በቀጣይነት ለማቅረብ ፈንዱን በማሢሢር ለመድሃኒት አቅርቦት ማስፋፊያና ማጠናከሪያ የሚሆን የህዳግና የአገልግሎት ክፍያ ተመኑ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

12.1 የተገላባጭ ፈንድ መድሐኒቶች እና የሕክምና መገልገያዎች የአገልግሎት ክፍያ

ሀ. ከአገር ዉስጥ ለሚገዙ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች

1. የአገር ዉስጥ አምራቾችን ለማበረታታትና ዋጋቸዉ ዉድ የሆኑትን ገበያዉን ለማረጋጋት እንዲቻል እንዲሁም ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ከአገር ዉስጥ ለሚገዙ መድሐኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ከህብረተሠቡ አቅም አኳያ ግምት ዉስጥ በማስገባት 10 በመቶ ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ማካካሻ በመጨመር የሚተመን ይሆናል፡፡

2. የአገር ዉስጥ አምራች ሆነዉ ኪሚካልና ሪኤጀንት የሚያመርቱ 10% ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ማካካሻ በመጨመር እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡

ለ. ከዉጭ አገር ለሚገዙ መድሐኒቶች

3. ከዉጭ አገር በአንጻራዊነት በዝቅተኛ ዋጋ ተገዝተዉ ለሚገቡ መድሃኒቶች 30% ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች መመለሻና ማካካሻ በመጨመር እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡

ሆኖም የመግዣ ዋጋቸዉ በተለያዩ ምክንያቶች ካለዉ የወቅቱ ገበያ አንፃር ሲወዳደር ዉድ የሆኑ መደሃኒቶች እንዲሁም የረጅም ጊዜ ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ተጠቃሚዎች የሚታዘዙ መድሃኒቶች በአብዛኛው የመክፈል አቅም የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍል በመሆናቸው እና የኤጀንሲው ተልዕኮም ለማሣካት የዋጋ ማስተካከያ በዚሁ መመሪያ ክፍል 7.2 በተቀመጠው አሰራር መሰረት ይደረጋል፡፡

12.2 የሕክምና መሳሪያዎች

ሀ. ከአገር ዉስጥ የሚገዙ የሕክምና መሳሪያዎች

ከአገር ዉስጥ የሚገዙ የሕክምና መሳሪያዎች 10% ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ማካካሻና መመለሻ በመጨመር ለጤና ተቋማት እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡

ለ. ከዉጭ አገር የሚገዙ የሕክምና መሳሪያዎች

የሕክምና መሳሪያዎች በባህሪያቸዉ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ በመሆናቸዉ የግዢ ዉስብስብነት እንዲሁም ከሚይዙት የመጋዘን ቦታና ተጨማሪ ወጪዎች አንጻር ከፍ ያለ የአገልግሎት ክፍያ መሆን የሚገባዉ ቢሆንም የጤና ተቋማት በጀት ግምት ዉስጥ በማስገባት እንደ ግዢ ዋጋዉ ወደ ጤና ተቋም የማድረስ፣ የመሳሪያ ተከላ፣ ስልጠና እና ኮሚሽኒግ ጨምሮ በሚከተለዉ መልኩ የአገልገሎት ህዳግ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

1. ከብር (10)አስር ሚሊየን በላይ የመግዣ ዋጋ ያላቸዉ የሕክምና መሳሪያዎች 7% የአገልግሎት ወጪ ምለሳ፡፡
2. ከብር አንድ ሚሊዮን እስከ ብር አስር ሚሊየን የመግዣ ዋጋ ያላቸዉ የሕክምና መሳሪያዎች 10% የአገልግሎት ወጪ ምለሳ፡፡
3. ከብር አንድ ሚሊየን በታች የመግዣ ዋጋ ያላቸዉ የሕክምና መሳሪያዎች 15% የአገልግሎት ወጪ ምለሳ፡፡

4. በፕሮግራም ገንዘብ ከተገላባጭ ፈንድ ላይ መድሃኒት ወይም የህክምና መሳሪያዎች በሚዛወርበት ጊዜ የስርጭት 7% በአጠቃላይ የዕቃ መደበኛ የመጋዘን ዋጋ ላይ በመጨመር ይሆናል፡፡

12.3 የጤና ፕሮግራም መድሐኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች የግዢና የስርጭት አገልግሎት ክፍያ

ከልማት አጋሮች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በኤጀንሲዉ በኩል ተገዝተዉ እና በዓይነት ገቢ ሆነዉ ለህብረተሰቡ በነጻ የሚከፋፈሉ የጤና ፕሮግራም መድሃኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎች የግዢና የስርጭት አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ፡-

ሀ) ለግዢ በመግዣ ዋጋ ላይ (FOB value) 2% ይሆናል፡፡

ለ) የማሰራጫ ወጪዉ ከመድሃኒቱ መግዣ ዋጋ (FOB value) 5% ይሆናል፡፡

ሐ) በዚሁ መመሪያ ክፍል 6.2 ሀ ና ለ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በበህሪያቸውና በምንጫቸው የተለዩ ቁሳቁሶች በኤጀንሲዉ እና በአጋር ድርጅቶች መካከል በሚደረጉ ውሎች መሰረት ይሆናል ፡፡

ይህ አሠራርና ክፍያ ኤጀንሲዉ ወደፊት ቀጣይ ጥናቶችን በማድረግ የግዢና የስርጭት ወጪዉን ለመሸፈን እንዲያስችል የአገልግሎት ክፍያ ክለሳ በማድረግ በማኔጅመንት ቦርድ ቀርቦ ሲፀድቅ ሊሻሻል ይችላል፡፡

ክፍል ሰባት

13. ዋጋ ማስተካከያ ስለማድረግ

ኤጀንሲው በአዋጅ የተሠጠውን ሃላፊነት ለመወጣት ጥራታቸዉንና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጡ መድሃኒቶች እና የሕክምና መገልገያዎችና መሣሪያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሠቡ ለማቅረብ፣ ብክነትን ለመቀነስ እንዲያግዘዉ በጣም ዉድ የሆኑ፣ ረዘም ላለጊዜ የሚወሰዱ መድሃኒቶች፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ የተቃረቡና እንደዚሁም አዝጋሚ የክምችት እንቅስቃሴ ያላቸዉ መድሃኒቶች በጥቅም ላይ ለማዋል የተገላባጭ መድሃኒት ፈንድ የዋጋ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

13.1. የመሸጫ ዋጋቸው ውድ የሆኑ መድኃኒቶች ፡-

ሀ. ዋጋቸዉ በጣም ውድ የሆኑ መድሃኒቶች ለህብረተሠቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርስ ለማድረግ እንዲቻል የተገላባጭ ፈንድ አቅም ግምት ዉስጥ በማስገባት በግዢ ትንበያና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ሰብሳቢነት የክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት እና የፈንድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በተዉጣጡ ባለሙያዎች አባል በሚሆኑበት ኮሚቴ ታይቶ በሚቀርብ የውሣኔ ሃሣብ መሰረትና በዋና ዳይሬክተር ሲፀድቅ የዋጋ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

ለ. ከላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴዉ በሚያቀርበዉ የዉሳኔ ሃሳብ ዉድ ከሆኑ መድሃኒቶች የሚቀነሰዉ ዋጋ ሌሎች በተነፃፃሪ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ እና የፍጆታ መጠናቸዉም ሰፊ በሆኑ መድሃኒቶች ለማጣጣት በሚያስችል መልኩ ይሆናል፡፡

13.2 የመክፈል አቅም የሌላቸው የህብረተሠብ ክፍሎች ለረጅም ጊዜ የሚወሠዱ መድሐኒቶች

ሀ. የረጅም ጊዜ ክትትል የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ በሽታዎች ማስታገሻ የሚወሠዱ መድሃኒቶች በአብዛኛው የመክፈል አቅም የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍል በመሆናቸው እና የኤጀንሲው ተልዕኮን ለማሣካት በኮሚቴዉ በሚቀርብ ጥናት ላይ በተመሠረተ መልኩ የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

ለ .በዚሁ መሰረት የስኳር ህሙማን የሚወስዱት ኢንሱሊን፣ ለካንሰር ህሙማን የሚሰጡ መድሃኒቶች፣ ለኩላሊት ንቅለ ተከላ የሚያገለግሉ መድሃኒቶች፣ ለአዕምሮ ህሙማን የሚዉሉ መድሃኒቶች… ወዘተ ላይ በዋና ዳይሬክተር ሲፀድቅ ያለህዳግ በተገዛበት ዋጋ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከተገዛበት ዋጋ ዝቅ ብሎ የማስተካከያ ዋጋ በመስራት ይቀርባል፤ ይህም ጉድለት በዘላቂነት በሌሎች መዲኃኒቶች ዋጋ ላይ የሚሸፈንበት አግባብ ሲኖረው፡ በሚንስቴሩና ለጋሽ አጋሮች ድጎማምም ይካካሳል፡፡

13.3 ገበያን ለማረጋጋት የሚቀርቡ መድኃኒቶች፤

ሀ. ህይወት አድን ሆነዉ በገበያ ላይ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸዉን መድሃኒቶች ገበያ ለማረጋጋት መድሃኒቶች በመንግስት ጤና ተቋማት፣ በከነማ መድሃኒት ቤቶች፣ በቀይ መስቀልና በማህበረሰብ ፋርማሲ በዋጋቸዉ ወይም የተወሰነ የትርፍ ህዳግ ብቻ ተጨምሮ እንዲሰራጩ በኮሚቴዉ ተጠንቶ ሲቀርብ፣ በዋና ዳይሬክተር ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

13.4 የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተቃረቡ መድኃኒቶች :-

ሀ. በተለያዩ ምክንያቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በመቃረቡ ምክንያት ወይም በገበያ ዘገምተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው መድኃኒቶችን በመለየት ዋነኛ እንቅስቃሴ ያለመኖሩ ምክንያት የዋጋ መወደድ ሆኖ ሲገኝ የመሸጫ ዋጋ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡ የክምችቱን ብዛትና ቀሪውን ጊዜ ግምት ዉስጥ በማስገባት ክምችቱ ዘገምተኛ እንቅስቃሴ ሲኖረዉ በኮሚቴ ተጠንቶ ሲቀርብና በዋና ዳይሬክተር ሲጸድቅ የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ለ. በመመሪያዉ በቁጥር 7.4.1 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሪ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ከ 20 እስከ 25 በመቶ ሲደርስ ዘገምተኛ መሆናቸዉን “Trend analyses” በመስራት እና በቀረው ጊዜ እንደማያልቁ የሚገመቱ መድኃኒቶቹ የአገልግሎት ክፍያን በማንሳት ለመንግስት ጤና ተቋማት ብቻ በዋጋዉ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

ሐ. በመመሪያዉ በቁጥር 7.4.1 እና 7.4.2 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቀሜታ ጊዜያቸዉ ከ 6 ወር በታች የቀረዉና ዘገምተኛ እንቅስቃሴ ስላላቸዉ እንደማያልቁ የሚገመቱ መድኃኒቶች የገበያውን ሁኔታ በማጥናት መድሃኒቶችን ጥቅም ላይ ሊያዉሉ ለሚችሉ የጤና ተቋማት የመጠቀሚያ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንዲጠቀሙበት በነፃ እንዲሠጥ ይደረጋል፡፡ በነፃ የተሰጠ መድኃኒት ወደ ኤጀንሲዉ አይመለስም፡፡ ስለአፈፃፀሙም ተገቢ ክትትል ይደረጋል፡፡

14. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የዋጋ አወጣጥ መመሪያ በስራ አመራር ቦርድ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

15. መመሪያዉን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ በቦርዱ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል።